# ሕይወት ያስከፈለ ሲኒማ

የ21 ዓመቱ ሲፕላል ማርዲ እና የ27 ዓመቱ ታፓን ሮይ በባንግላዲሽ ጌታችንን የሚያገለግሉ ክርስቲያኖች ነበሩ:: ጁላይ 29/2005 እኩለ ለሊት ላይ ወደሚወዱት ጌታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት በክብር ተጓዙ:: ሥንብታቸው ድንገተኛ ና ዘግናኝ በመሆኑ ለሚወዷቸው ሁሉ አስደንጋጭ ነበር:: ከማንም ጋር ጠብ አልነበራቸውም የተላለፉትም ሕግም የለም:: ወጣቶቹ በጨቤ ተወጋግተው የተሰውት የኢየሱስ ክርስቶስን የምድር ሕይወትና አዳኝነት የሚተርክ ፊልም በማሳየታቸው ነበር:: ከአካባቢው የእስልምና ት/ቤት ሃላፊ ፊልሙን ማሳየት እንዲያቆሙ ሁለት ጊዜ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው በኋላ ነው የተገደሉት::

የዘላለም ሕይወት የሰጣቸውን አምላካቸውን እያገለገሉ፤ ለአካባቢያቸውም ይሄን መልካም ዜና እያበሰሩ ሳሉ በወጣትነታቸው እቺን የክፋት አለም ተሰናበቷት:: የምድር ዘመኑን የሚያውቅ አንድም የለም:: ጥሪው ሲመጣ በቅጽበት እያንዳንዱ ሰው በጌታ ፊት ይቆማል:: ለሠራው ብቻ ሳይሆን ለተናገረው ሁሉ መልስ ይሰጥበታል:: ማቴ12:36 ሮሜ14:12

እናም ለዚህ ግፍና ግድያ እንኳ በገዳዮቹ ላይ እርግማን ለማውረድና ፍርዳቸውን መተመን አይጠበቅብንም:: ለፍርድና ለበቀል ክርስቶስ አልጠራንምና ነው:: አሳዳጆችንና ገዳዮችን በፍቅሩ እያንበረከከ ወደ መንግሥቱ መልሷቸው ሕይወታቸውን እስኪሰጡት ድረስም ሲያገለግሉት አይተናልና:: ስለሟቾቹ ወንድሞቻችን ግን አንድ ነገር እናውቃለን:: ተቃዎሚዎቻቸውም ሆነ አሳዳጆቻቸው በስጋቸው እንጂ በነፍሳቸው ላይ አንዳችም አቅም የላቸውም:: እናም ነፍሳቸው በሰላምና በሃሴት በእግዚአብሔር መንግስት ትገኛ ለች:: መጽሐፍ ቅዱስ «በጌታ ሆነው የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው::» ራዕ14:13 እንደሚል በክርስቶስ ሆኖ መሞት ትርፍ አለው:: ስለጌታ የታረዱ ሁሉ ነጩን ልብሳቸውን ለብሰው በበጉ ሠርግ ግብዣ ላይ እናገኛቸዋለንና ስለነሱ ብዙም የምንለው የለንም:: ይልቁንም በምድር ላይ ስላሉት ገዳዮቻቸውና ወደፊትም ለመግደል በልባቸው ለሚያደቡት የፍቅር ጥሪ አለን:: ጨቤና ሳንጃ የሚጨብጡበትን እጃቸውን ከደም ወደሚያነፃው እግዚአብሐር እንዲዘረጉት:: በጥላቻና በበቀል የተሞላ ልባቸውንም ኃጢአትን ሁሉ ይቅር ወደሚል ጌታ በንሰሃ እንዲያፈሱት በጌታ ፍቅር እንለምናቸዋለን:: «እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደእኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ»ያለ ጌታ በጥላቻ፣ በበቀልና በፍርድ የተሞላ ልባቸውን አውጥቶ በፍቅርና በርህራሄ ይሞላቸዋል::

የእግዚአብሔር ቃል «ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰገዳይ ነው» እንደሚልም ገና በልባቸው ለሚሸምቁም እግዚአብሔር በአምሳሉ ለፈጠረው ሰው ፍቅር እንዲያድርባቸው እንጸልያለን::

«ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቀውም፣እግዚአብሔር ፍቅር ነውና::» እንደሚል መመሪያችን



« ኃጢአትን ሁሉ ይቅር ወደሚል ጌታ ኑ እንላቸዋለን::»

ከጥላቻ ሰንሰለት ይፈቱ!!

ለእኛ ስደት የክርስትና አንዱ ክፍል እንጂ፣ወደረኞቻችን እንደሚያስቡት ከክርስቶስ እቅፍ የሚያወጣን አይደለም::ለዚህ ነው በብዙ ስደት የኖረውና በኋላም በስደት ወደ ጌታው የተሰበሰበው ሐዋርያው ጳውሎስ «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል?መከራ ወይስ ጭንቀት፣ወይስ ስደት፣ወይስ ራብ፣ ወይስ ራቁትነት፣ወይስ ፍርሃት፣ወይስ ሰይፍ ነውን?» በማለት የእግዚአብሔርንና የእኛን የማይፋቅ ቁርኝት ያረጋገጠው::

ክርስቶስን ተቀብለን አዲስ ሕይወት ስንጀምር:- «ለራሴ ሞቼ ለክርስቶስ እኖራለሁ...» ብለን ነውና በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለን፣ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን:: ከእኛ አንድ ስነኳ ለራሱ የሚኖር የለምና፣ለራሱም የሚሞት የለም::

**ለእኛ ስደት የክርስትና አንዱ ክፍል እንጂ፣ወደረኞቻችን እንደሚያስቡት ከክርስቶስ እቅፍ የሚያወጣን አይደለም::**

